# የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ
## ጠቅላይ ጽ/ቤት
## Catholic Bishops' Conference of Ethiopia (CBCE)
## General Secretariat/ECS
አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia

☎ (251) 11-155 03 00
Tel fax (251)11-155 31 13
✉ 2454

E-Mail: CBCE@cbce-gs.org
cbce.ecs@gmail.com
website: www.cbce-gs.org


ቀን ሐምሌ 26, 2014
Date:
ቁጥር CBCE/GS/288/22
Ref:

# የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ጳጳሳት መልዕክት

"በአንድ ልብ ሁኑ፥ በሰላም ኑሩ፥ የፍቅርና የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል።" 2 ቆሮ. 13:11

**ለመላው ኢትዮጵያውያን ካቶሊካውያንና በጎ ፈቃድ ላላችሁ ሁሉ**

## መግቢያ

እኛ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጳጳሳት 53ኛ መደበኛ ጉባኤያችንን ከሐምሌ 13-15 ቀን 2014 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ በጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት አዳራሽ አድርገናል። ሁልጊዜ እንደምናደርገው በዚህ ጉባኤያችን ስለቤተክርስቲያናችን፣ ስለጳጳሳት፣ ስለ ካህናት፣ ስለደናግል፣ ስለምዕመናን እና ስለሀገራችን ሠላም ጸሎት አድርገናል።

በሀገራችን ባለው ሁኔታ በመካከላችን ሊገኙ ስላልቻሉ ጳጳሳት ለብፁዕ አቡነ ተስፋሥላሴ መድህን እንዲሁም በአዲግራት ሰበካ ስለሚገኙ ካህናት ደናግልና ምዕመናን ጸሎት አድርገናል። እንዲሁም በህመም ላይ ለሚገኙት ለብፁዕ አቡነ ፀጋዬ ቀነኒና ውጭ ሀገር ለሚገኙት ለብፁዕ አቡነ አብርሃም ደስታ ጸሎት አድርገናል። በችግር ውስጥ ለሚገኙ የጳጳሳት ጉባኤ አባላት የሚደረገው ወንድማዊ ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አቅጣጫ አስቀምጠናል።

1. በጉባኤያችን መሠረታዊ በሆኑ የቤተክርስቲያናችን ሐዋርያዊ ጉዳዮች እና ቤተክርስቲያን ለሐዋርያዊ ሥራዎቿ ያሏት ዕድሎችና ፈተናዎችን ገምግመናል። በተለይ የካቶሊካውያንን ሁሉ ድምፅ ያዳመጥንበት የሲኖዶስ ጉዞ ከየሀገረ ስብከቱ የተሰበሰቡ ሪፖርቶች በብሔራዊ የሲኖዶስ አስተባባሪ



+ Cardinal Berhaneyesus D. Souraphiel, C.M. Metropolitan Archbishop of Addis Ababa, President of the CBCE, Chairman of Ethiopian Reconciliation and Peace Commission; Fr.Teshome Fikre (PhD), Secretary General
Please do not address your reply to a particular individual but to CBCE General Secretariat

ኮሚቴ ተጠናቅሮ ቀርቦ በእርሱም ላይ ከየሰበካው ከተገኙ ካህናት፣ ከደናግልና ምዕመናን፣ እዲሁም ወጣቶች ጋር ተወያይተን የቀረቡ ኃሳቦችን ወደ ተግባር መለወጥ እንዲቻል የቤተክርስቲያናችን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ እንዲዘጋጅ ብሔራዊ ኮሚቴ አዋቅረናል።

ቤተክርስቲያናችን በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስን የምታዳምጥ አባላቶቿ እርስ በእርሳቸው የሚደማመጡ፣ የሚከባበሩ፣ የሚተጋገዙ፣ አብረው የሚያቅዱ፣ አብረው የሚሠሩ፣ ያለፉትን ፈተናዎች በጥልቅ በወንድማማችነትና በእህትማማችነት መንፈሳዊነት አርመን ውጤታማ ሐዋርያዊ አገልግሎት የምንሰጥበትን ሁኔታ እንድናመቻች አቅጣጫ አስቀምጠናል።

2. ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊ ሥራዋን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንድታከናውን ዕንቅፋት እየሆነባት ያለውን በተለይ የሀገራችን የሠላም ማጣት ሁኔታ ትልቅ ፈተና ተደቅኖባታል። አዲግራት ሀገረ ስብከትን ጨምሮ ብዙ ሰበካዎቻችን የፈተናው ተጋሪዎች ናቸው። ካህናት ገዳማውያን በፀጥታ ምክንያት ገዳማቸውን ለቅቀው የተሰደዱ፣ የተዘጉ ጸሎት ቤቶችና ገዳማት ከጊዜ ወደጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ ነው።

   ዜጎች በነፃነት እንዲኖሩ ሕይወታቸው ዋስትና እንዲያገኝ መንግሥት እና ሕዝብ በጋራ በመሥራት በሀገራችን ሠላም እንዲሠፍን አበክረን እንጠይቃለን፡ ዛሬም በትግራይ የሚገኙ ወገኖች በፈለጉት መንገድ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር ሊገናኙ አልቻሉም። መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማግኘትም እየተቸገሩ ይገኛሉ። ዜጎች አሁንም በብዙ ቦታዎች (ለምሳሌ በወለጋ) በማንነታቸው ምክንያት እየተገደሉና እየተሰደዱ ነው።

   ከአሁን በፊት በተከታታይ እንዳደረግነው አሁንም ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የሠላምና የውይይት ብሎም የእርቅ አማራጭ ላይ እንዲያተኩሩና ለዚሁም መሳካት ሁላችንም የበኩላችንን ጥረት እንድናደርግ ጥሪ እናቀርባለን፡ ሊጀመር የታሠበው የፖለቲካ ድርድር በውጤት እንዲጠናቀቅ በጸሎት እንደግፋለን። የተጀመረው ሀገራዊ ውይይት እንዲሳካም ቤተክርስቲያናችን የራሷን ጥረት ታደርጋለች።

3. በድርቅ የተጎዱ ወገኖቻችንም የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ እንዲያገኙ እያሳሰብን የተቻለውን ሁሉ ጥረት እንዲደረግ ቤተክርስቲያናችንም የበኩሏን አስተዋፅኦ አጠናክራ ትቀጥላለች።

4. የኢትዮጵያ ጳጳሳት ጉባኤ አባላትና የቤተክርስቲያን ተወካዮች በታንዛኒያ ዳሬ ሰላም ከተማ ከሐምሌ 2 እስከ ሐምሌ 10 ቀን 2014 ዓ.ም. በተከናወነው

የምሥራቅ አፍሪካ የጳጳሳት ጉባኤዎች ህብረት ጠቅላላ ጉባኤ ተሳትፈዋል፡፡ በዚህ ጉባኤ የምሥራቅ አፍሪካ ጳጳሳት በቅዱስ አባታችን አቡነ ፍራንቸስኮስ "ውዳሴ ለአንተ" በሚለው ሰነድ በመመርኮዝ የአካባቢ ጥበቃ በሰው ልጅ ሕይወት ላይ እያሳረፈ ያለውን ተፅዕኖ በተመለከተ በጥልቀት ተወያይተው አቅጣጫ አስቀምጠዋል፡፡

ቤተክርስቲያን ተፈጥሮን የመንከባከቡ ኃላፊነት ከስብከተ ወንጌል ሥራ በተጓዳኝ የሚሠራ በመሆኑ ሁሉም ካቶሊካዊ እና በጎ ፍቃድ ያላቸው ሁሉ ሀገር በቀል ዛፍን በየተቋማቱ፣ በየቤቱ በመትከል፣ የአካባቢ ንፅህናን በመጠበቅ፣ ወንድማማችነትንና እህትማማችነትን የበለጠ በማጠናከር፣ በሠላም ግንባታ ሥራዎች በቅንነት በመሳተፍና በተፈጥሮ ያለው መስተጋብር እንዲጠናከር ቤተክርስትያናችን ኃላፊነቱን እንድትወጣ አቅጣጫ አስቀምጠናል፡፡ በሀገራችን መንግሥት እና ሕዝብ እየከናወነ ያለው ተፈጥሮን የመንከባከብ ንቅናቄ ትልቅ ዕድል በመሆኑ ሁላችንም በፍቅር እንድንሳተፍ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነየሱስ
የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ጳጳሳት ጉባኤ
ሐምሌ 2014 ዓ.ም.
አዲስ አበባ